በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን

# ለ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለትምህርትና ቅስቀሳ የተዘጋጀ ተጨማሪ መመሪያ

ለሕዝብና ቤት ቆጠራ መሣካት ሁላችንም እንተባበር!

## በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
## የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን

# ለ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ
# ለትምህርትና ቅስቀሳ የተዘጋጀ
# ተጨማሪ መመሪያ

**ለሕዝብና ቤት ቆጠራ መሣካት ሁላችንም እንተባበር!**

7. ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ እመጣጥ ቀስበቀስ ነበር። ወታደሮችን ለመመልመልና፣ ግብር ለማስከፈል ሲባል በ17ኛው ዘመን ይከናወን የነበረው የሕዝብ ቆጠራ ሥራ መልኩንና እጹሙን በመለወጥ ሌሎች የሕዝቡን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ እርእስቶችን በመጨመር ይካሄድ ጀመር። ለምሳሌ ስለአስተዳደር፣ ስለንግድ ሥራ፣ ስለትምህርት፣ ለምርምር የሚጠቅሙ መረጃዎችን፣...ወዘተ. ያዘሉ ጥያቄዎችን የሕዝብ ቆጠራው ይጨምር ጀመር። ይህንንም ዓላማ በመከተል በተለያየ ጊዜ የሕዝብ ቆጠራዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሃገሮች ተካሂዷል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በኩቤክ .................... | በ1660 /እ.ኤ.አ./ | ቆጠራ | ተካሂዷል። | |
| በሲውድን .................... | በ1749 | " | " | " |
| በዩናይትድ ስቴትስ ........... | በ1790 | " | " | " |
| በእንግሊዝና ፈረንሳይ ......... | በ1801 | " | " | " |
| በናይጄሪያ .................. | በ1863 | " | " | " |
| በካናዳ .................... | በ1871 | " | " | " |
| በጋና ...................... | በ1891 | " | " | " |
| በሩሲያ .................... | በ1897 | " | " | " |

8. እነዚህ ሃገሮችና ሌሎችም በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ክፈለ ዘመንና ከዚያም በፊት ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ ያካሄዱና የሚያካሂዱት አገሮች በአሁኑ ዘመን በየአምስት ወይም በየ10 ዓመቱ ቆጠራ ያካሂዳሉ። /ለምሳሌ በየአምስት ዓመቱ ቆጠራ የሚያደርጉ አገሮች ካናዳ፣ አየርላንድ፣ ኩዌት፣...ወዘተ./

## III. ዘመናዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም

9. የሕዝብና ቤት ቆጠራ አጠር ባለ ሁኔታ ሲገለጽ በተወሰነ ወቅትና በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር ውስጥ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስለአለው ሕዝብና ስለሚገኙት ቤቶች ብዛት፣ ስለ ሕዝቡ የዲሞግራፊ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ከአነስተኛ የአስተዳደር ክልል ማለትም ከገበሬ ማህበር ወይም ከቀበሌ ማህበር ጀምሮ እስከ ብሄራዊ ክልል ከዚያም በሀገር አቀፍ ደረጃ በገጠርና በከተማ መረጃዎችን ያስገኛል።

## IV የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሄድ መሟላት ያለባቸዉ ዋና ዋና ጉዳዮች

10. የቆጠራዉ ሥራ በጣም አስፈላጊ፣ ከፍተኛ ሥራና ወጪ እንደዚሁም የድርጅቶችና የግለሰቦች ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ የሚከናወነዉ በመንግሥት ነዉ። ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የቆጠራዉ ሥራ በአዋጅ መደገፍ ስላለበት የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ማዉጣት ያስፈልጋል፣

11. ቆጠራዉ አንድ ወሰኑ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ዉስጥ ያለዉን አካባቢ ሳይደጋገም ወይም ሳይዘለል ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። ወሰኑ የታወቀ የአስተዳደር ክልል ማለትም ወረዳ፣ ከተማ፣ ዞን፣ ብሄራዊ ክልል ወይም ሀገርን ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልል ማለት ነዉ።

12. ቆጠራዉ ወሰኑ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ነዋሪ የሆነዉን ሕዝብና በክልሉ የሚገኘዉን ቤት ሁሉ ሳይደገምና ሳይዘለል የሚያጠቃልል መሆን አለበት፣

13. በቆጠራዉ የሚሰበሰበዉ መረጃ እያንዳንዱን ነዋሪ በነፍስ ወከፍ በየቤቱ ሄዶ በመጠየቅ የሚገኝ መልስ መሆን አለበት። ይኸም ማለት የቀበሌዉን ባለሥልጣን ወይም የመንደር ኃላፊዉን ብቻ በመጠየቅ ስለቀበሌዉ ወይም ስለመንደሩ ነዋሪዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች መሰብሰብ አይኖርበትም ማለት ነዉ፣

14. ቆጠራዉ አንድ የተወሰነ ቀንና ሰዓትን በማስመልከት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ መጠናቀቅ አለበት። ይኸዉም ቆጠራዉ በአንድ በተወሰነ ቀን በእኩለ ሌሊት በቤተሰቡ የተገኙትን አባላት ወይም በዚያ ሰዓት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት የነበሩትን ብቻ ያጠቃልላል። በመሆኑም

የሕዝቡን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ባሕርያት የሚገልጹ መረጃዎችን በተመለከተ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል ማለት ነዉ።

25. በአንድ አስተዳደር ክልል ሆስፒታል ለመሥራትና የተሩትንም የጤና አገልግሎቶች ለነዋሪው ለመስጠት በክልሉ የሚኖረውን ሕዝብ ብዛት ማወቅ አስፈላጊ ነው። እንደዚሁም ትምህርት ቤቶችን ለመሥራት በቂ አስተማሪዎችንም ለማሰልጠን በዚሁ ክልል በትምህርት የዕድሜ ክልል ዉስጥ ያሉትን ሕጻናት ብዛት ማወቅ ያስፈልጋል። ነገር ግን የሕዝቡን ብዛት ብቻ ቆጠራው ቢገልጽ በትምህርት የዕድሜ ክልል ዉስጥ ያሉትን ሕጻናት ወይም በሥራ ዕድሜ ያሉትን ኅልማሳዎች አያመለክትም። ስለዚህ በልዩ ልዩ ዕድሜ ያሉትን ግለሰቦች ብዛት ለማወቅ በቆጠራው ጊዜ የግለሰቦች ዕድሜም ይጠየቃል። ከዚህም በላይ ለሕብረተሰቡና ለኢኮኖሚው ልማት ለሚተለሙት ፕሮዥዎች ሁሉ የሕዝቡን ብዛት ማወቅ ብቻ በቂ ስላልሆነ በተጨማሪ የሕዝቡን ልዩ ልዩ የሶሻልና የኢኮኖሚ ባሕሪያትን የሚያመለክቱ እንደ ጾታ፣ ኃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ብሄረሰብ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፍልሰትን ሁኔታ፣ የትምህርት ችሎታ፣ የሥራ ዓይነት፣ የተወለደበት ሥፍራ፣ የተወለዱት ልጆች ብዛት፣ የሞቱት ሰዎች ብዛት፣...ወዘተ. መረጃዎች በሕዝብና ቤት ቆጠራ ጊዜ ይሰበሰባሉ።

26. በኢትዮጵያ በ1987 ሊካሄድ የታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያበረክት ጥርጥር የለውም። ለሐገሪቱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅድ ለማዘጋጀት እንዲሁም ለአስተዳደር ጉዳዮች ከሕዝብና ቤት ቆጠራው ውጤት የሚገኘው መረጃ መሠረታዊ መነሻ ይሆናል።

27. የሕዝቡን የሥርጭት ሁኔታ ማለትም በየትኛው ሥፍራ ምን ያህል ሕዝብ እንደሚኖር የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ከአለ መንግሥት የአስተዳደር ክልሎችን በሚገባ እንዲያደራጅ ይረዳዋል። ይህም ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ለምሳሌ ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ መንገዶችን፣ የውሃ ልማትን፣...ወዘተ. ለማስፋፋት ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ከቆጠራው ሥራ የሚገኘው መረጃ ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች አንዱ ለአስተዳደር ሥራ እንዲረዳ የምርጫ ክልሎችን ለይቶ ለማወቅና እንዲሁም የመራጮችንና የተመራጮችንም ብዛት በተመለከተ ግንዛቤ በመስጠት ሕዝባዊ ምርጫ ለማካሄድ ይረዳል። ይህም ስለሆነ የሕዝቡን ጂኦግራፊያዊ ሥርጭት በተመለከተ ዝርዝር መረጃው በትክክል መታወቅ አለበት።

28. ድርቅና ረሃብ ያጠቃቸውን አካባቢዎች ለወደፊት ዘለቄታ ባለው መንገድ ለማቋቋምና መፍትሄ ለማስገኘት የሕዝቡ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት በሚገባ መታወቅ አለበት። ከዚህም በላይ ብዙ የልማት ፕሮጀክቶች በሃገሪቱ ውስጥ የተካሄዱና የሚካሄዱም አሉ። እነዚህ የልማት ፕሮጀክቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት በአንዳንድ በተወሰኑ ቦታዎች ነው። እነዚህም ፕሮጀክቶች በሚካሄዱባቸው ቦታዎች የሕዝቡን ብዛት፣ ስርጭት እና የሕዝቡን ጥንቅር የሚያመለክቱ መረጃዎች በሕዝብ ቆጠራው አማካይነት ሊገኙ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት መረጃዎች ፕሮጀክቶች ለሚካሄዱባቸው ሥፍራዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው። ከዚህ ቀደም የአንዳንድ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች በሚካሄድባቸው ሥፍራዎች የእስታቲስቲክስ መረጃዎች ይሰበሰቡ ነበር። ይህም የሥራ ድርብርቦሽን፣ የሰው ጉልበትና የገንዘብ መባከንን ስለሚያስከትል ለድርጅቶችም ሆነ ለግለሰቦች በሕዝብና ቤት ቆጠራ ሳቢያ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ሁሉ ቢሰበሰቡ የሥራ ድርብርቦሽና አለአስፈላጊ የሆነ ወጭዎችንም ለማስወገድ ይችላል።

29. የሕዝብና ቤት ቆጠራው የሃገሪቱን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች ለማጥናትና ለመመዘን ከዚያም የነዚህን አቋም ለማጠንከርና ለማሻሻል በሚያስችሉ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ይረዳል። ይህም የሠራተኛ ቅጥር ጥያቄና የሰው ጉልበትን የማደራጀት ፕሮግራሞችን ለመቀየስ፣ ስለሕዝብ ፍልሰት፣ ስለቤቶች ችግር፣ ስለትምህርት፣ ስለጤና አጠባበቅ፣ ስለሕዝቡ ማሕበራዊ ደህንነትና ስለ ማሕበራዊ ኀልጋሎት፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ዕቅድን ለማዘጋጀት እንደዚሁም ሌሎችን ለነዋሪው የሚጠቅሙ በርካታ ጉዳዮች በሚገባ ለማከናወን ሕዝቡን በሚመለከት ትክክለኛና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

30. በሕዝብና ቤት ቆጠራው ተግባር የሚሰበሰበው መረጃ ያለፈውን፣ የአሁኑን፣ የወደፊቱን፣ የሕዝብ ብዛትና ዕድገት፣ የሕዝቡን ስርጭትና የሕዝቡን በፆታና በዕድሜ አመዳደብ በሚመለከት ትንተናና ግምገማ ለማካሄድ ይረዳል። እንዲሁም የከተሞች ዕድገትና የጂኦግራፊያዊ ስርጭት በሥራ ዓይነትና በትምህርት ደረጃ፣ የሕዝቡን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ባሕሪያት የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደ ጾታና የዕድሜ አመዳደብ፣ በልዩ ልዩ ሕብረተሰብ መካከል ስለአለው የልደትና የሞት ልዩነት፣...ወዘተ. ለምርምርና

ለጥናት እንዲሁም ለማህበራዊና ለኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ለመዘጋጀትና በተጨማሪም የንግድን ዕድገት በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመሻትና በሚገባ እቅድንም ለመምራት ዓይነተኛ መግሪያ ይሆናል።

31. ከዚህ በላይ የተገለጹት ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች ከሚሰጡት ጥቅሞች ሌላ መረጃዎቹ ለግለሰቦችና እንዲሁም በንግድ በኢንዱስትሪና በግብርና ለተሠማሩ ድርጅቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ተፈላጊ የሆኑ የንግድ ዕቃዎችንና ሸቀጣ ሸቀጦችን ገምቶ ለተለያዩ ሸማቾች ለማቅረብና ፍላጎታቸውንም ለማርካት የሕዝቡን ብዛት በዕድሜና በጾታ እንዲሁም በሥርጭት ሁኔታ በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል። የንግድ ድርጅቶችንና እንዱስትሪዎችን ለማቋቋም በትክክል ቦታው አማካይ እንደሆነ፣ የሰው ጉልበት ይገኝ እንደሆነ፣ የመጓጓዣ ጥርጊያ መንገዶች መኖራቸውን በትክክል ማረጋገጥ አስፈላጊ ነዉ። ከዚህም በላይ አንዳንድ ግለሰቦች ጥናትና ምርምር ለማድረግ ፍላጎት ካላቸዉ ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኘው መረጃ በሚገባ ሊረዳ ይችላል።

32. በሕዝብና ቤት ቆጠራው አማካይነት የሚሰበሰቡት መረጃዎች ወደፊት በናሙና የሚካሄዱ /በከፊል ለሚካሄዱ/ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጥናቶችን ለማከናወን መሠረት ከመጣሉም በላይ እስታቲስቲክስ ነክ ለሆኑ መረጃዎች መሠረት ነው። ከዚህም ሌላ ከሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቆጠራዎች በተለይ የኢንዱስትሪና የእርሻ ነክ ቆጠራዎች ከሚደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ብዙ ትምህርትና ልምድ ማግኘት ይቻላል።

33. ከሕዝብና ቤት ቆጠራው የሚገኙት መረጃዎች ለሃገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ከመስጠታቸዉም በላይ በዓለም አቀፍ ደረጃም ጥቅም ያስጣል። ይኸውም ስለአፍሪካና ስለዓለም ሕዝብ ዕድገት /በዓመት ከመቶ ስንት እንደሚያድግ ለማወቅ/ለሚከናወነው ጥናት ጠቃሚ ነው።

iii. <u>በቆጠራው የሚሠማራዉ የሰዉ ኃይል ብዛት</u>

34. የሁለተኛዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከመጀመሪያዉ /ከ1976 ቆጠራ/ ጋር ሲነፃፀር በሕዝብ ብዛትና በሚሸፈነዉ አካባቢ የላቀና ሰፊ በመሆኑ የሚያስፈልገዉ የሰዉ ኃይል ቁጥር ከፍተኛ ነዉ። የቆጠራዉ ትድመ ዝግጅት አካል የሆነዉን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ካርታ ሥራ መ/ቤቱ ለ17 ወራት ባካሄደዉና በተዘጋጁት የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ካርታዎች ብዛት መሠረት 84,900 የሚሆኑ/ 68,250 ቆጣሪዎች 13,650 ተቆጣጣሪዎች እንዲሁም 3,000 የሚሆኑ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የቆጠራ ጽ/ቤት ሠራተኞች በቆጠራዉ ሥራ ይሳተፋሉ ተብሎ ይገመታል።

iv. <u>በቆጠራዉ የሚሸፈነዉ አካባቢ</u>

35. ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በመሠረቱ ቆጠራዉ በሚካሄድበት አገር ያለዉን ሕዝብና ቤት ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። በመሆኑም በ1987ቱ ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልል የሚገኙትን የዘላን ሕዝቦችን ጭምር ለመሸፈን ታቅዷል።

v. <u>ቆጠራውን የሚያካሄደው ማን ነው ?</u>

36. በአዋጅ ቁጥር 8/1980 ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድ እንደሚችል ተገልጿል፣ ሆኖም የሕዝብና ቤት ቆጠራን የማካሄድ ተግባር በጣም ግዙፍና ከባድ እንዲሁም ከፍተኛ ወጪንና ብዛት ያለው የሰው ኃይል ስምሪት የሚያስፈልገው ሥራ ከመሆኑ የተነሣና ይህንን ተግባር ለማስፈጸም የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችን፣ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን፣...ወዘተ. ከፍተኛ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ ስለሆነ የቆጠራው ሥራ የሚካሄደው በአዋጅ ቁጥር 32/1985 በተቋቋመ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ነው። የተቋቋመው ኮሚሽን በርካታ መ/ቤቶችን ያካተተ ሲሆን የማዕከላዊ ስታቲስታክስ ባለስልጣን የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላል።

VII. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ</u>

37. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የአገሪቷ አንደኛው ብሄራዊና ከፍተኛ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም እንደመሆኑ መጠን በአንድ ድርጅት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል በቅድሚያ ግንዛቤ አግኝቶ ለዚሁ ሲባል የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች በተቀናጀ መልክ ለማሳተፍ እንዲቻል የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ማውጣት ያስፈልጋል።

38. በ1976 የተከናወነውንና በአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሕጋዊነት ለማረጋገጥና በአዋጁ መሠረት የተቋቋመውን ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት ዕውን ለማድረግ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ቁጥር 252/1976 ታውጆ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ በጥቅምት ወር 1987 ሊካሄድ ለታቀደው ለሁለተኛው ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 32/1985 ጥቅምት 8 ቀን 1985 ታውጇል። በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው ኮሚሽን በግምባር ቀደምትነት ቆጠራውን ለማስፈጸም አግባብ ያላቸውን መ/ቤቶችና ድርጅቶች በማስተባበር የቆጠራው ሥራ እንዲከናወን ያደርጋል። በአዋጁ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቆጠራውን በማቀድና በማደራጀት እንዲሁም ተግባራዊ እንዲሆን በአስፈጻሚነት ዓይነተኛ ሚና እንድሚጫወት ተገልጿል። በአዋጁ መሠረት የተቋቋመው ኮሚሽን የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት አመቺ በሚሆንበት መንገድ ከብሄራዊ ደረጃ አንስቶ እስከ ወረዳ ድረስ በኮሚሽኖችና በጽ/ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን ከወረዳ በታች ደግሞ ባሉት አስተዳደር ክፍሎች በኮሚቴ ደረጃ ተዋቅራል።

VIII. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራዉ ሥራ መዋቅር</u>

39. የሕዝብና ቤት ቆጠራውን ዕቅድ ማውጣት፣ ማደራጀትና የቆጠራውንም ተግባር ከግቡ ለማድረስ ከፍ ያለ ብሄራዊ ድጋፍን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶችና አንዳንድ ድርጅቶች ሙሉ ድጋፋቸውንና ትብብራቸውን ማበርከት ይኖርባቸዋል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት የተለያዩና አግባብ ያላቸው ሚ/ር መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ያቀፈና በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ማዕከላዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ተቋቁሟል በተዋረድም ይኸው ኮሚሽን በክልልና በዞኖች ቀደም ብሎ የተቋቋመ ሲሆን በወረዳ ደረጃም ኮሚሽኖቹ በቅርቡ ተቋቁመዋል። እንዲሁም በማዕከል፣ በሁሉም ክልሎችና ዞኖች የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤቶች የተቋቋሙ ሲሆን በወረዳ ደረጃም ጽ/ቤቶች በቅርቡ ተቋቁመዋል። ከወረዳ በታችም በከተሞች፣ በቀበሌ ማሕበራትና በገበሬ ማሕበራት ደረጃም የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ።

40. በየደረጃው የተዋቀሩት ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች ቆጠራውን ለማስፈጸም በየደረጃው የቆጠራው ሥራ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት፣ አመራር በመስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ በመውሰድ፣ ስለቆጠራው አፈጻጸም የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና ቆጠራው በታቀደው ጊዜ መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠበቃል።

IX. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራዉን ለማካሄድ የተከናወኑ አበይት ቅድመ ዝግጅቶች</u>

i. <u>የቆጠራ ዕቅድ ዝግጅት</u>

41. ካለፈዉ የቆጠራ ልምድ በመነሳትና በአሁኑ ቆጠራ ወቅት የሚኖሩትን ሁኔታዎች በማገናዘብ ቆጠራዉን ለማካሄድ የሚያስችል ዕቅድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት አቅርቧል። የስምምነት ሰነዱ ይዘት የቆጠራዉ ዓላማና ጥቅም ቆጠራዉን ለማካሄድ መከናወን ያለባቸዉ የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ተግባሮች ዝርዝር፣ የቆጠራዉ አፈጻጸም፣ በቆጠራዉ የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚጠናቀሩበትን ዘዴ፣ ቆጠራዉን ለማካሄድ የሚያስፈልገዉ የሰዉ ኃይልና የበጀት ፍላጎት ያጠቃልላል።

ii. <u>የዉጭ ዕርዳታ ስለማግኘት</u>

42. ለቆጠራዉ ተግባር ማስፈጸሚያ ከመንግሥት ከሚመደበዉ በጀት በተጨማሪ ከዉጭ ዕርዳታ በማስፈለጉ ስለቆጠራዉ ፕሮጀክት የስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በመበተንና በዉጭ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አማካይነት ስብሰባ በመጥራት የተወሰኑት ቆጠራዉን ለመርዳት ቃል

በመኪና ሊገባ በፍጹም የማይቻልባቸውን ቦታዎች ... ወዘተ ነበር። ከ30ዎቹ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች 19 በገጠር የሚገኙ ሲሆን 11 ደግሞ በከተማ የሚገኙ ናቸው።

57. በዚህ የናሙና ቆጠራ ወደ 30,000 ቤተሰቦች የተሸፈኑ መሆኑ የተገመተ ሲሆን ቆጣሪዎችን በማሠልጠን፣ መጠይቆችን በማረምና በማሻሻል፣ በቆጣሪዎችና በተቆጣጣሪዎች መመሪያዎች ውስጥ የታዩ ግድፈቶችና ሊሻሻሉ የሚገባቸው መመሪያዎችን በማረም፣ መጠይቆችን ለመሙላት የሚወስደውን ጊዜ በማወቅና ሌሎችም በዋናው ቆጠራ ወቅት ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ነገሮች በማወቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም መሠረት ሊሻሻሉ ወይም ሊስተካከሉ የሚገባቸዉ ሁሉ ተሻሽለዉና ተስተካክለዉ ለዋናዉ ቆጠራ ተዘጋጅተዋል።

vii. <u>የሠራተኞች ምልመላ፣ ሥልጠናና ሥምሪት</u>

58. ከላይ የተጠቀሱትን በቆጠራው የሚሠማሩ ሠራተኞች መመልመልና ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስችላቸውን ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም በቆጠራዉ ሥራ ለሚሠማራዉ የሰዉ ኃይል በሦስት ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት ዕቅድ ወጥቷል። በዕቅዱም መሠረት፣

ሀ. በመጀመሪያ ዙር ሥልጠና ማለትም በአሠልጣኞች ሥልጠና የሚሣተፉ ወደ 200 የሚደርሱ ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል የማ/ስ/ባ ባልደረቦች በዋናዉ መ/ቤት የ10 ቀናት ሥልጠና ከሐምሌ 13/1986 ጀምሮ ተሠጥቷል።

ለ. በሁለተኛ ዙር ወደ 3,600 ለሚደርሱ አሰልጣኞች በክልልና በዞን ደረጃ ሥልጠና እንዲሰጥ ታቅዶ ወደ 1,200 ለሚደርሱ በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የመስክ ሠራተኞች ከነሐሴ 2/1986 ጀምሮ የአሰልጣኞች ሥልጠና የተሠጠ ሲሆን በተመሳሳይ ደረጃ ለተቀሩት 2,400 ለሚደርሱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ደግሞ ከመስከረም 2/1987 ጀምሮ በየክልሉና በየዞኑ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል።

ሐ. በሦስተኛ ዙር በዋናዉ ቆጠራ ሥራ ላይ የሚሠማሩ 12ኛን ክፍል ያጠናቀቁ ወደ 68,250 የሚደርሱ ቆጣሪዎችን መመልመልና ማሠልጠን፣ እንዲሁም እነኚህን ቆጣሪዎች የሚቆጣጠሩ ወደ 13,650 የሚደርሱ መምህራንና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የመመልመል የማሠልጠንና ለቆጠራዉ ሥራ የማሰማራቱ ሂደት ይቀጥላል።

በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ ዙር በአሠልጣኝነት የሠለጠኑት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል እንዲሁም የመስክ ሠራተኞች በዋናዉ ቆጠራ ለሚሠማሩ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች አሠልጣኝ ከመሆናቸዉም በላይ በክልል በዞንና በወረዳ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በመሆን የቆጠራዉን ሥራ እንዲያስተባብሩ ተመድበዋል።

X. <u>በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት</u>

59. ሊካሄድ በታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በገጠርና በከተማ በአብዛኛው ተመሳሳይ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ቢሆንም የቤት መረጃን አስመልክቶ በገጠርና በከተማ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማንፀባረቅ ሲባል ከከተማ አኗኗር ጋር የሚጣጣሙ አንዳንድ ጥያቄዎች በከተማ ቆጠራ እንዲካተቱ ተደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከቤት ቤት በመሄድ ሰፋ ያለ መረጃ መሰብሰብ ብዙ ወጪና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ በሚደረገው ቆጠራ አጭር መጠይቅ በመጠቀም የተወሰኑ መረጃዎች ለሁሉም ቤተሰቦች ከቤት ቤት በመዘዋወር የሚሰበሰቡ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎችን ግን ረዥም መጠይቅ በመጠቀም በናሙና ለተመረጡ ቤተሰቦች ብቻ ከቤት ቤት በመዘዋወር ይሰበሰባሉ።

ሐ. <u>በዕለቱ ቤት የነበሩ እንግዳ፥</u> በቆጠራው ዕለት ማለትም ጥቅምት 1 ቀን/1987 ቆጠራው በሚካሄድበት ቤት ውስጥ በሚገኘው ቤተሰብ መደበኛ የቤተሰብ አባል ሳይሆን በእንግድነት የተገኙ ሰዎች በዚሁ ቤተሰብ ሥር በዕለቱ ቤት የነበሩ እንግዳ ተብለው ይቆጠራሉ።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ በቆጠራው ዕለት በእንግድነት የሚገኙ ሰዎች ሁሉ መደበኛ አባል ከሆኑበት ቤተሰብ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው በዕለቱ በቤት ያልነበሩ ነዋሪ ሆነው ሲቆጠሩ በእንግድነት ከሚገኙበት ቤተሰብ ጋር ደግሞ እንደ እንግዳ ሆነው ይቆጠራሉ። ስለሆነም አንድ ቤተሰብ ከላይ የተገለጹትን ሶስቱን የነዋሪ ሁኔታዎች ወይም ሁለቱንም የነዋሪ ሁኔታዎች ወይም አንዱን ሁኔታ የሚያሟሉ ግለሰቦችን በቆጠራው ዕለት ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ በተጠቀሰው ቤተሰብ ውስጥ በቆጠራው ዕለት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሙሉ ተገኝተው በተጨማሪም በእንግድነት ግለሰቦች ሊገኙ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ከመደበኛ የቤተሰብ አባላት በቆጠራው ዕለት ከመኖሪያ ቤታቸው ሳይገኙ በሌላ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት እንግዳ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ።

69. <u>እንግዳ፥</u> በዚህ ቆጠራ እንግዳ ማለት ጥቅምት 1ቀን/1987 በተገኘበት ቤት ወይም ቤተሰብ መደበኛ ነዋሪና መደበኛ አባል ያልሆነ ግለሰብ ነው። በተጨማሪ የራሱ መኖሪያ ቤትና ቤተሰብ ያለው ግለሰብ በቆጠራው ዕለት የተገኘበት ቤት ውስጥ ወይም ቤተሰብ ጋር በተከታታይ ሲኖር ከስድስት ወራት ካልበለጠው ይህ ግለሰብ በተገኘበት ቤተሰብ እንግዳ ይባላል።

70. <u>የጋርዮሽ መኖሪያ፥</u> ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ አኗኗር ውጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት እየኖሩ በቤቱ ወይም በቤቶቹ ያሉትን መገልገያዎች ማለት ውኃን፥ መብራትንና ሌሎች አገልግሎቶችን በጋራ ወይም በሕብረት የሚጠቀሙበትና በአንድ መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ ወይም የግለሰብ ድርጅት የሚኖሩበት ቤት ወይም ቤቶች የጋርዮሽ መኖሪያ ይባላል።

የጋርዮሽ መኖሪያ ሆቴሎች፥ ሆስፒታሎች፥ ወህኒ ቤት፥ የሕፃናት ማሳደጊያ፥ የአእምሮ በሽተኞች መታከሚያ፥ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፥ የወታደር ካምፖች። ያረጁ ሰዎች መጦሪያ፥ የጸባይ ማረሚያዎች፥ አድባራትና ገዳማት፥ የሥራ ካምፖች፥ ...ወዘተ. ያጠቃልላል። እዚህ ላይ ሆቴሎችንና ሆስቴሎችን በሚመለከት መታወቅ ያለበት ነጥብ፥ አንድ ግለሰብ ሌላ ቦታ መኖሪያ ቤት ኖሮት በቆጠራው ዕለት ሆቴሉ ወይም ሆስቴሉ ውስጥ ቢገኝ፥ ወይም ሆቴሉ ወይም ሆስቴሉ ውስጥ ሲኖር ስድስት ወር ካልሞላው ይህ ግለሰብ የሚቆጠረው የሆቴሉ ወይም የሆስቴሉ እንግዳ እንጂ የሆቴሉ/የሆስቴሉ ነዋሪ ተብሎ አይደለም።

በጋርዮሽ መኖሪያ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦች ከጋርዮሽ መኖሪያ ግቢ ለብቻቸው ወይም ከቤተሰብ ጋር ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች አኗኗር እንደመደበኛ ቤተሰብ በመሆኑ የሚቆጠሩት እንደመደበኛ ቤተሰብ ነዋሪ ይሆናል።

71. <u>መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች፥</u> በእግር መንገድ፥ በመኪና መንገዶች ዳር፥ በተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፥ በቤተክርስቲያንና በመስጊዶች ቅጥ፥ በመቃብር ቤት እና በመሳሰሉት ቦታዎች ተኝተው የሚያድሩ ሰዎች መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች ይባላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ተኝተው የሚያድሩበት ቦታ የተወሰነ ላይሆን ይችላል። የሚካሄደው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ያጠቃልላል።

72. <u>ዕድሜ፥</u> እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደሆነ ተጠይቆ ይመዘገባል። ስለዚህ ዕድሜ ምን ማለት እንደሆነና እንዴት በትክክል ሊታወቅ እንደሚችል እያንዳንዱ ግለሰብ ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ዕድሜ ሲባል አንድ ሰው ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ እስከሚቆጠርበት ዕለት (እስከ ጥቅምት 1/1987) ድረስ ያለውን ጊዜ በሙሉ ዓመት ማለት ነው። ሙሉ ዓመት ማለት የአንድ ሰው ዕድሜ የተወሰነ ዓመታት ሆኖት በተጨማሪም ከአንድ ዓመት የሚያንሱ ወሮች ካሉበት ወሮቹን ትቶ ሙሉ ዓመታቱን ብቻ መውሰድ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ልጅ ዕድሜው 13ዓመት ከ11 ወር ከ3 ሳምንት ከሆነ የሚወሰደው የልጁ ዕድሜ 13 ዓመት ብቻ መሆኑን ነው። የሰውየው ዕድሜ በዓመት በወርና በሳምንት ከተሰጠ ዕድሜው በሙሉ ዓመት ብቻ ይመዘገባል። አንድ ሕፃን ልጅ ከአንድ

80. የትምህርት ሁኔታ፣ በቆጠራው ወቅት ከሚሰበሰቡት የሕዝብ ማኅበራዊ ባሕሪያት አንዱ የሕዝብን የትምህርት ሁኔታ የሚመለከት ይሆናል። ይኸውም ዕድሜው አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ በመማር ላይ መሆኑ፣ አሁን በመማር ላይ ካልሆነ ደግሞ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤት ገብቶ ተምሮ የሚያውቅ ወይም የማያውቅ መሆኑንና አሁን በመማር ላይ ከሆነ የሚማርበትን የክፍል ደረጃ የሚያመለክቱ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። አንድ ግለሰብ በመማር ላይ ነው የሚባለው በመደበኛ ትምህርት ቤት፣ በዩኒቨርስቲ፣ በኮሌጅ፣ በማሠልጠኛ ተቋም፣ በቄስ፣ በቁርዓን ወይም በሌሎች አንስተኛ የትምህርት ዝግጅት (ካሪኩለም) ባለው የትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ በመማር ላይ ሲሆን ነው። የቤተሰብ አባል ማንበብና መጻፍ የሚችል ከሆነ አሁን በመማር ላይ ቢሆንም ባይሆንም የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ደረጃን በሚመለከት መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

አንድ ግለሰብ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መጻፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ኃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ አረፍተ ነገሮችን ብቻ ማነብነብ የሚችሉ ሁሉ የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም።

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል የሚጠየቀው የማንበብና የመጻፍ ችሎታ አለን ያሉትን ሁሉ ሲሆን ይህም አሁን በመማር ላይ ያሉና ከዚህ በፊት የተማሩትንም ያጠቃልላል። የጨረሱት ክፍል ሲባል ግለሰቦች ባለው የትምህርት ሥርዓት ያጠናቀቁትን ከፍተኛ የትምህርት ክፍል የሚያመለክት ነው። ይኸም በክፍል ወይም በደረጃ ሊለካ ወይም ሊተረጎም የሚችል ሆኖ ማንኛውም በመደበኛ ትምህርት ወይም በዩኒቨርሲቲ የሚካሄድ ትምህርትና እንዲሁም ከዚህ ውጭ በማሠልጠኛ ተቋሞችና በመሳሰሉት የሚካሄደውን ትምህርት ያጠቃልላል።

81. የሥራ ሁኔታ፣ በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሐከል የኢኮኖሚ ሁኔታን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይገኛሉ። ይኸ መረጃ የሚሰበሰበው ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ መደበኛ አባላት ነው። ይኸ ጥያቄ በገጠር ዕድሜው አሥር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት 12 ወራት ለምን ያህል ጊዜ ምርታማ ሥራ መሥራትና አለመሥራቱን፣ ከሠራ ለምን ያህል ጊዜ፣ የሥራው ዓይነት፣ የሚሠራበት ድርጅት፣ ካልሠራ ደግሞ ያልሠራበትን ምክንያት ሲጠየቅ በከተማም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ዕድሜው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት ሰባት ቀናት ምርታማ ሥራ መሥራቱንና ስንት ቀን እንደሠራ ይጠየቃል።

ምርታማ ሥራ ማለት የሥራው ውጤት የሆነውን ሸቀጣ ሸቀጥ አገልግሎት በገንዘብም ሆነ በዕቃ በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። በራስ፣ በቤተሰብ ይዞታ፣ በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በግለሰብ ድርጅት በቀን፣ በሳምንት፣ በወር ወይም በሠሩበት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ሲሠሩ ነው።

82. ልደት፣

በቆጠራው ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሀከል ልደትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይገኛሉ። ልደትን በሚመለከት የሚጠየቁ የቤተሰብ አባላት ዕድሜያቸው አሥር ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶች ሲሆን ጥያቄውም መውለድ ከጀመሩ በጠቅላላው ሕይወት ኖሮአቸው የወለዷቸዉ ልጆች ስንት እንደሆኑና ባለፉት 12 ወራትም በሕይወት የተወለዱ ልጆች ካሉ ስንት እንደሆኑ ነው። እዚህ ላይ "ሕይወት ኖሮዋቸው የተወለዱ" ማለት አንድ ሕፃን እንደተወለደ ሕይወት ያለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ሕይወት ኖሮአቸው የተወለዱ ልጆች ብዛት በውርጃና በሞት የተወለደውን አይጨምርም።

ii. <u>ስለእያንዳንዱ ቤት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በተመለከተ:-</u>

በብሄራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሕዝቡን ብዛትና ስርጭት፣ የሕዝቡን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መሰል ባሕሪያትን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆን ስለ ቤቶች ብዛትና ስለሚሰጡት አገልግሎት እንዲሁም ስለመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ መረጃዎችንም ለማስገኘት ጭምር ነው። ይህን መረጃ በትክክል ለመሰብሰብ እንዲቻል በቅድሚያ " ቤት፣ የቤት አገልግሎት፣ የመኖሪያ ቤት መገልገያዎችና ክፍል" የተባሉት ፅንሰ ሀሳቦች ምን ማለት እንደሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል።

83. <u>ቤት</u> ፣ ቤት ማለት በአሠራሩ ተለይቶ "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅቱ ብቻ የሚያገለግል ነው።

ሀ. <u>የቤቱ አሠራር የተለየ ነው</u> የሚባለው ዙሪያውን በግድግዳ፣ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ በመሆኑ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ሲሆን ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሳጠራ፣ በፕላስቲክ፣ በካርቶን፣ ... ወዘተ. ግድግዳው የተሠራ ወይም የተከበበና ጣራው በፕላስቲክ ክዳን የተሸፈነ ሆኖ ቁመቱና የወለሉ ስፋት በጣም ያነሰ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል። ይኸ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንጻር ሲታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል።

ለ. <u>የቤቱ አሰራር ራሱን የቻለ ነው</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ ደረጃ፣ መሬት... ወዘተ. የራሱ መግቢያና ወይም መውጫ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው ቤት መውጫ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው።

84. <u>የቤቱ አገልግሎት</u> በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል። የአገልግሎት ዓይነቶች፣

ሀ. ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ
ለ. ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት
ሐ. ለሆቴል/ሆስቴል
መ. ሌላ ጋርዮሽ
ሠ. ለድርጅት ብቻ ናቸዉ።

85. የቤቱ አገልግሎት ዓይነት ትርጉም፣

ሀ. <u>ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ</u>፣ በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የዋለ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ" ይባላል።

ለ. <u>ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት</u>፣ በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያና ለድርጅት" ይባላል። ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የሶሻል ወይም የኢኮኖሚ ተቋም ነው። ይኸውም የማምረቻ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ጫማ፣ ዳቦ፣ ጨርቃ ጨርቅ ... ወዘተ. አምራቾች፣ የጫማ እድሳት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሕግ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎትና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የሚያካሂዱትን ሁሉ ያጠቃልላል። ስለሆነም የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚባለው በአንድ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባላት እየኖሩበት እዚያው ውስጥ

ii. <u>መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት እንዴት ነዉ?</u>

99. መረጃዉን የሚሰበስበዉ ቆጣሪ በተመደበበት የቆጠራ ቦታ ከቆጠራዉ ቀን ጀምሮ በሚሰጠዉ የቆጠራ ካርታ መሠረት በመጀመሪያ የቤት የቤተሰብና የድርጅቶችን ምዝገባ ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ያከናዉናል። ምዝገባዉ የሚያገለግለዉ በቆጠራ ቦታዉ ክልል ዉስጥ ያሉ ቤቶችና ቤተሰቦች ሳይደገሙ/ሳይዘለሉ መቆጠራቸዉን ለማረጋገጥ ነዉ። ቆጣሪዉ ይህንን ሲያደርግ በቤቱ በራፍ በሚታይ ቦታ በጠመኔ የ"X" ምልክት ያደርጋል። ምዝገባዉ ከተጠናቀቀ በኋላ ምዝገባዉን ባከናወነበት ሁኔታ ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ዝርዝር የሕዝብና ቤት መረጃዎችን ይሰበስባል።

100. የሕዝብና ቤት ቆጠራዉ ኢትዮጵያን በሙሉ የሚሸፍን ሲሆን በቆጠራዉም የሚጠቃለሉት በቆጠራው ጊዜ የነበሩት ነዋሪዎች ማንም ሰው ሳይዘለል /ሳይቆጠር እንዳይቀር/ ወይም በድጋሚ ሳይቆጠር መሆን አለበት። በቆጠራው እያንዳንዱ ግለሰብ ተለይቶ ከተመዘገበ በኋላ ስለ ግለሰቡ የሚገልጹ እንደ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ብሄረሰብ፣ ሃይማኖት፣...ወዘተ. መረጃዎች ይመዘገባሉ። ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ግለሰብ በቆጠራው የሚሸፍነው በአንድ በተወሰነ ቀን ማለትም የቆጠራውን ቀን (ጥቅምት 1ቀን 1987) መሠረት በማድረግ ሲሆን በዚህም መሠረት የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት በዚያን ቀን የነበረውን ሁኔታ ነው።

iii. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሆዎች፣</u>

101. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ እንደ ማንኛውም ሳይንሳዊ ጥናት ሁሉ በትክክል መሠራት አለበት። አንድ ልብስ ሰፊ ሸሚዝ፣ ሱሪ፣ ቀሚስ ለመስፋት ብትትን ጨርቅ ከመቆራረጡ በፊት የሚሰፋላቸውን ሰዎች ልክ መውሰድ ወይም መቀየስ እንደሚገባው ለማንም ግልጽ ነው። ልብሱ የሚሰፋላቸውን ሰዎች ልክ ካልወሰደ የሚሰፋው ሸሚዝም ሆነ ሱሪ ወይም ቀሚስ ለሰዎቹ በልካቸው አይሆንላቸውም፣ ማለት ሊሰፋ፣ ሊጠብ ወይም ሊረዝም፣ ሊያጥር ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ መንግሥት ለሕዝቡ አስፈላጊና በቂ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሀገሪቷና በየአስተዳደር ክፍሉ የሚገኘውን የሕዝብ ብዛትና ባሕሪያት ማወቅ አለበት። ይኸውም የነዋሪውን ሕዝብ ብዛት በጾታ፣ በዕድሜ ማለትም ምን ያህል ሕጻናት፣ ልጆች፣ አዋቂዎች እንዳሉ፣ ምን ያህል የተማሩ፣ ያልተማሩ፣ እንዲሁም ለተማሩት የትምህርት ደረጃቸዉ፣ ከሕዝቡ ምን ያህሉስ ሥራ እንዳለዉና ስንቱስ ሥራ ፈት እንደሆኑ ... ወዘተ በትክክል በማወቅ የሚሰጠዉ አገልግሎት ሳያንስ ወይም ሳይትረፈረፍ እንዲሰጥ ለማድረግ ይረዳዋል። ይህም ሊሆን የሚችለው የሕዝብ ቆጠራ ሥራ በትክክል የተካሄደ ሲሆን ነው። ስለዚህ የሚከተሉት ሁለት <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሆች</u> በማንኛውም ጊዜ ቢሆን መዘንጋት የለባቸውም።

102. <u>የመጀመሪያዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትዕዛዝ ማንኛውም የቤተሰብ አባል መቆጠር አለበት</u> የሚለዉ ነዉ። ምንም እንኳ አንድ የቤተሰብ አባል በጣም ያረጀ ወይም ሕጻን ቢሆንም መቆጠር አለበት። አንዳንድ ጊዜ የሚጠቡ ሕጻናት፣ በጣም ያረጁ ሰዎች፣ አእምሮአቸው ትክክል ያልሆኑ ሰዎች፣...ወዘተ. ሳይቆጠሩ ሊዘነጉ ይችላሉ። ግን ይህ በማንኛውም ጊዜ መሆን የለበትም። ማንኛውም ሰው የሕዝብ ቆጠራው ተግባር በሚከናወንበት ወቅት በአካል ዓይን መታየት ስለአለበት ማንም ሰው ከቆጠራ መዘንጋት የለበትም። ማስታወስ የሚገባን የዛሬዋ ወይም የዛሬው ሕጻን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ትምህርት ቤት መግባታቸውን ነው። ዛሬ ካልተቆጠረ በመማር ዕድሜ የሚገኙት ሕጻናት ብዛት በትክክል ስለማይታወቅ መንግሥት ትምህርት ቤት ለመሥራት፣ አስተማሪ ለማሰልጠን፣...ወዘተ. ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት ችግር ሊገጥመው ይችላል። ከዚህም በላይ መገንዘብ የሚገባን የዛሬ ሕጻናት የነገ አዋቂዎች እንደሚሆኑ በመረዳት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በሚካሄድበት ጊዜ አንድም ሕጻን የአንድ ደቂቃ፣ የአንድ ሰዓት፣ የአንድ ቀን ወይም የአንድ ወር ዕድሜ እንኳ ቢኖረው ከቆጠራው መገለል እንደሌለበት ነዉ።

103. በአንድ ቡና ተክል አንድን የቡና ዛፍ ብቻዉን ተክል ለማለት አይቻልም። እያንዳንዱን የቡና ዛፍ በማጠቃለል ብዙዎቹ የቡና ዛፎች በአንድነት የቡና ተክል ይባላሉ እንጂ። በትምህርት ቤትም የአንድን ክፍል ተማሪዎች የሚመሠርቱት በክፍሉ የሚገኘዉ እያንዳንዱ ተማሪ ነዉ። እንደዚሁም በሕዝብና ቤት ቆጠራ ወቅት በአንድ ቤት የሚኖር እያንዳንዱ ግለሰብ አንድ ቤተሰብን ይመሠርታል። እያንዳንዱ

ቤተሰብ ደግሞ የአንድን ከተማ ወይም የአስተዳደር ክፍል ሕዝብ በመመሥረት የአስተዳደር ክፍሎችም ተጠቃለዉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይመሠርታሉ። ስለዚህ ትክክል የሆነ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማከናወን አንድም ግለሰብ ከቆጠራው መገለል የሌለበት መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው።

104. ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርህ <u>አንድ ሰው ሊቆጠር የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚለዉ ነዉ።</u> ይህም ማለት ማንም ግለሰብ ሁለት ጊዜ ወይም ሶስት ጊዜ ሊቆጠር አይገባዉም ማለት ነዉ። ስለዚህ እነኚህ ሁለት መርሆች ምንጊዜም ቢሆን መታወስ አለባቸው።

ሀ. ማንኛውም ሰው መቆጠር አለበት።
ለ. ማንኛውም ሰው አንድ ጊዜ ብቻ ነው መቆጠር ያለበት።

iv. <u>ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙት መረጃዎች በሚስጥር የሚጠበቁ ስለመሆናቸዉ።</u>

105. ከእያንዳንዱ ግለሰብ በመረጃ ሰብሳቢው አማካይነት የሚሰበሰበው መረጃ በሚስጥር የተጠበቀ ይሆናል። ይህም ማለት በመረጃ ሰብሳቢውም ሆነ በሌሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሠራተኞች የተሰበሰቡት መረጃዎች የግለሰብ መረጃዎችን በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ለማንም እንዳይገለጽ መንግሥት በጥብቅ ይቆጣጠራል። በዚህም መሠረት በመረጃ ሰብሳቢውም ሆነ ማንኛውም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሠራተኛ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በቃልም ሆነ በጽሁፍ እንዳይገለጽ ሕግ ያግዳቸዋል።

106 የዚህም ሕግ ዋና አላማው እያንዳንዱ ግለሰብ መረጃ ወይም ለሚቀርቡለት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጥያቄዎች መልስ በሚሰጥበት ወቅት ምንም ዓይነት ፍርሃት ወይም ጥርጣሬ እንዳይገባው ለማድረግ ነው። የቆጠራው ዓላማ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚሰጠውን መረጃ ነጥሎ በማውጣት ማሳየት ሳይሆን የብዙ ግለሰቦችን መረጃዎች በአጠቃላይ የሚመለከት መረጃዎችን ማቅረብ ነው። ለምሳሌ ያህል በደሴናው በአንድ ከተማ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች እንዳሉ፣ በጾታ፣ በዕድሜ ለማመልከት ነው እንጂ በከተማው ነዋሪ የሆኑት አቶ እገሌ ስንት ልጆች እንዳሉዋቸው፣ የሰውየውን ስም ወይም እድሜአቸውን፣...ወዘተ. መረጃው አያመለክትም። ስለዚህ በጠቅላላው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት የግለሰብን መረጃ ነጥሎ በማዉጣት ሪፖርት አይቀርብም።

v. <u>ቆጠራዉ እንዲሳካ ከህብረተሰቡ የሚጠበቅ ትብብር</u>

107. የቆጠራዉን ሥራ በተሳካና በተቀላጠፈ መልኩ ዳር ለማድረስ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ትብብር ወሣኝ ነዉ። ይህ ደግሞ የእያንዳንዳችንን ጥረት የሚጠይቅ ነዉ። ምክንያቱም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በግሉ ሊወጣዉ የማይችል ሥራ በመሆኑ ሁሉም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቤተሰቦችና እንዲሁም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዚህ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ከፍተኛ ትብብር ማድረግ አለባቸዉ።

የቆጠራዉ ሥራ ግብ መምታት በተለይ የሚወሰነዉ በእያንዳንዱ የአገሪቱ ነዋሪ ጽኑ ፍላጎት ነዉ። ከእያንዳንዳችን የሚፈለገዉ በጣም ቀላል ነገር ነዉ። ይኸዉም።

1. ቆጣሪዎች ለቆጠራዉ ሥራ ወደየቤታችን ሲመጡ እቤት በመገኘት አስፈላጊዉን ትብብር ማድረግ በተለይ ለሚጠይቁን ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ መሆን፣

2. ለሚጠየቁት ጥያቄዎች የምንሰጠዉ ምላሽ ለአገር ግንባታ፣ ለልማት ዕቅዶች፣ ለሕዝብ ጠቀሜታ የሚዉል መሆኑን ተረድተን እዉነተኛ መልስ መስጠት፣

3. ስለቆጠራዉ ለጎረቤቶቻችን ለጓደኞቻችን እንዲሁም ለዘመዶቻችን ማስረዳት፣ በተለይ ላልተማሩት ወገኖች መፈክሮቹ ተለጣፊ/ተንጠልጣይ ወይም የሚበተኑት ወረቀቶች ምን እንደሚሉ ማብራራት ናቸዉ።

